በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ጥር 3 ቀን 2011
አዲስ አበባ
ጋዜጣዊ መግለጫ

## የመከላከያ መማክርት (ካውንስል) ዛሬ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ውይይት አደረገ።

መከላከያ ሠራዊት በህጋዊ ማዕቀፎች፤ በአደረጃጀት፤ በመፈጸም ብቃትና በትጥቅ በከፍተኛ የለዉጥ ጎዳና ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። ይህን ልዉጥ በሁሉም ደረጃ ተፈጻሚ ከማድረግና ወደ ታች ከማዉረድ አንጻር የተገኙ ተጨባጭ ዉጤቶች፤ የታዩ ክፍተቶችና ቀጣይ አቅጣጫዎች ዉይይት ተደርጎባቸዋል። ዉይይቱን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ የመሩት ሲሆን፤ መከላከያ እስካሁን ያደረጋቸዉ የተቋማዊ ሪፎርም ስራዎች ምን ያህል ርቀት እንደተጓዙ በመገምገም በቀጣይ ትኩረት ሊሰጣቸዉ የሚገባ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ አስቀምጠዋል።

የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ቴክኖሎጂን የሚታጠቅ፤ በራሱ አቅም መጠገን፤ ማሳደግ ብሎም መፍጠር የሚችል እንዲሆን በርካታ የአቅም ግንባታ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ መከላከያ ከቴክኖሎጂ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለውና እንደሌሎች አገራት ከራሱም አልፎ ለሌሎች የቴክኖሎጂ ዘርፎች ምንጭ መሆን የሚችል የቴክኖሎጂ ማዕከል እንዲሆን እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ተገምግመዋል። በሁሉም ደረጃዎች የሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦች ተዋጽኦ የጠበቀ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትም ተገምግመዋል።

ከዚህም ባሻገር የሀገሪቱን ወቅታዊ ውስጣዊና ከባቢያዊ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ የሠራዊት አሰፋፈር እንዲኖር የተጀመረመው እንቅስቃሴ ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን፤ በዚህም የመከላከያ ሠራዊት አሰፋፈር ወቅታዊ ፤ተጨባጭና ታሳቢ ስጋትን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚከናወን በመሆኑ ሕብረተሰቡም በዚህ መልኩ እንዲረዳው ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ተነስቷል። የሠራዊት እንቅስቃሴው እንደ አዲስ ከማስፈረም ባሻገር ለረዥም ጊዜ በድንበር ምሽግ ውስጥ የነበሩ የመከላከያ አባላትን ወደ ሥልጠናና አቅም ግንባታ ሥራዎች ማስገባት የአጠቃላይ ተቋማዊ ሪፎርሙ አካል በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ሁሉም አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ ተላልፏል።

በሁሉም ረገድ መልካም የአፈጻጸም ጅምሮች እንዳሉ የገመገመው መማክርቱ፤ በቀጣይ እነዚህን ለውጦች አጠናክሮ ለመቀጠል የሚስችሉ ሥራዎችን እንዲሰሩ አቅጣጫዎች አስቀምጧል።

//